


<u>እድሜህን ንገረኝ</u>

አርቀህ ብታይም  እስኪደክም አይንህ
ተሰፋ ብትራብም እስኪነጋ ቀንህ

አጥንቶችህ ላልተው መቆም ቢያቅትህም
አባባ ማሙሼ እድሜህን አትደብቅ አላወራብህም

አይንህ ይናገራል እድሜህ ከፍ ያለ ነው
የዛሬ አልጨነቀህ ልብህ ነገ ላይ ነው።

ዱቄት ተስፍሮልህ ዱቄት ላይ ቁጭ ብለህ
ለማትወጣ ነፍስህ ሂድ መለስ እያለህ

እድሜህን ንገረኝ ማሙሽ አትደብቀኝ
እኔም የበኩሌን የምነግርህ አለኝ።

ሳምሶን ተፈራ
December 20, 2005